**የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ በአገሪቱ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎችንና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማትን ለማሳደግ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር የኢፌዴሪ የሳይስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ ገለፁ።**

ሚኒስትሩ ይህንን የተናገሩት በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት "ወደ እውቀት-መር ኢኮኖሚ" በሚል መሪ ቃል ከሐምሌ 5 እስከ 8 /2013 ዓ.ም የተካሄደው የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ምርምር፣ ቴክኖሎጂ እና የኢንዱስትሪ ትስስር ኮንቬንሽን (HEART CONVENTION 2021) ይፋዊ የማጠቃለያ ስነስርዓት በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚው ቅጥር ግቢ በተካሄደበት ወቅት ነበር።

ሚኒስትሩ አያይዘዉም፣ አካዳሚው በዋነኛነት እየሠራበት ያለው ሳይንስን ባህል በማድረግ በእዉቀት፣ በክህሎት እና በጥበብ የበለጸገ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር መደራደር የሚችል ማህበረሰብ የመፍጠር ተግባር ወሳኝነት እንዳለው አስገንዝበዋል።

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ በበኩላቸው፣ ሀገራችን ጥንታዊ ምድረ ቀደምት ብትሆንም፣ ሳይንስን ለኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግልጋሎት የማዋል ልምዳችን አናሳ መሆኑን አስታውሰው፤ በርካታ ገጸበረከቶቻችንን ተጠቅመን መበልጸግ የሚያስችለንን የሳይንስ ዕውቀትና ባህል ለማዳበር የዘርፉ ተመራማሪዎችና ምሁራን የድርሻቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ታሪካዊ ቅርሶች እና ልዩ ልዩ ሀገር በቀል እጽዋት ያሉበትን ግቢ ለኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የሰጠው በልዩ እይታ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይኸውም ቅርሶች በአግባቡ እንዲጠበቁና አካዳሚው የኢትዮጵያ ምሁራን ሳይንሳዊ ምርምር ሥራዎች ማበልጸጊያ ማእከል እንዲሆን ታስቦ መሆኑን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጽጌ ገብረማርያም ስለ አካዳሚው በሰጡት ማብራሪያ፣ አካዳሚው የማኅበረሰቡን አኗኗር ለማሻሻል፣ በሁሉም መስክ አገራዊ እድገትና ብልጽግና እንዲመጣ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ፣ የሳይንስ እውቀትና ባህል በኅብረተሰብ ዘንድ ለማስረጽና መንግሥት በጥናት በተረጋገጡ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ጠቃሚ ፖሊሲ እንዲያወጣ ለመደገፍ የተቋቋመ የምሁራን ቤት መሆኑን ገልጸዋል።

"ዛሬ ከሳይንስ ውጭ የሆነ ነገር የለም" ያሉት ፕሮፌሰሩ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ማኅበረሰብ የተሳሰሩ በመሆናቸው ሳይንስን ባህል ያደረገ ትውልድን ለመፍጠር አካዳሚው ሰፊ ሀገራዊ ራእይ ሰንቆ እየሠራ በመሆኑ፣ መንግሥትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ድጋፋቸውን አጠናክረዉ ሊያስቀጥሉ ይገባል ብለዋል።

የአካዳሚው ዋና ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ተከተል ዮሐንስ በበኩላቸው፣ አካዳሚው ለአገሪቱ ልማት ጠቀሜታ ያላቸውን የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን ለመሥራት የአካዳሚው አባላት በስድስት የተለያዩ መስኮች ተከፍለው የጥናትና ምርምር ስራዎችን እየሠሩ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

ከነዚህ በተጨማሪ በተለያዩ አካዳሚያዊ እና ሳይንሳዊ ርእስ ጉዳዮች ላይ የኅብረተሰቡን ሳይንሳዊ ግንዛቤ ለማሳደግና ሳይንሳዊ አሠራሮችን ለማጎልበት ወርሐዊ የሳይንሳዊ ገለፃና ውይይት መድረክ በማዘጋጀት በሳይንሳዊ እሳቤዎች የሚመራ ንቁ ኅብረተሰብ ለመፍጠር እየሰራ መሆኑንም ፕሮፌሰር ተከተል አብራርተዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሙሉ ነጋ አወያይነት በተካሄደ፣ ውይይት ከኮንቬንሽን 2021 የተወሰዱ ልምዶች፣ መሻሻል ያለባቸው አሠራሮች እና የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚን አቅም ለማጎልበት መደረግ ስላለባቸዉ ተግባራት እንዲሁም የቀጣዩ ዓመት ኮንቬንሽን በአካዳሚው ቅጥር ግቢ እንዲካሄድ የሚሉ አስተያየቶች ከተሳታፊዎች ተሰጥዋል።

በዚሁ መሰረት ኮንቬንሽን 2022 በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ቅጥር ግቢ ዉስጥ እንዲካሄድ አስፈላጊዉ ሁሉ እንደሚደረግ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ የስራ ሓላፊዎች ገልጸዋል።

በማጠቃለያ መርሃ ግብሩ ለዘንድሮው ኮንቬንሽን (CONVENTION 2021) መሳካት ጉልህ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የዕውቅና የምሥክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል።

ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመርሃ ግብሩ ማጠቃለያ ባደረጉት ንግግር፣ በቀጣይም ሳይንስን ባህል በማድረግ በእውቀት፣ በክህሎት፣ በመልካም ሥነ ምግባር እና በጥበብ የበለጸገ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሃገራችን ምሁራን ሙያዊ ሓላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አስተላልፈዋል።